# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY
PUBLIC SCHOOLS

---

**ተዛማጅ ምንጮች:** IQA-RA, IQB-RA, IQD, IQD-RB, JEE
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት:** Office of Teaching, Learning, and Schools

## በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አትሌቲክስ ለሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የአካዳሚ ብቁነት

### I. ዓላማ

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ለሚሳተፉ ተማሪዎች ስርአት አቀፍ የአካዳሚክ ብቁነት መመሪያዎችን በዝርዝር መግለጽ

### II. ዳራ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ትምህርት ማህበር እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መካከል በተዘረዘረው ስምምነት መሠረት ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በማንኛውም የአትሌቲክስ እንቅስቃሴ መሳተፍ ለሚመርጡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስታይፔንድ (stipend) ይህ ደንብ የሚጠቀምበትን የአካዳሚ ብቁነት ደረጃ ይበይናል። በተጨማሪም፣ በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከአትሌቲክስ ውጭ ሌሎች እንቅስቃሴዎች ይኖራሉ ተብሎ ይጠበቃል፣ በዚህም የአካዳሚክ ብቃታቸው ምንም ይሁን ምን ለሁሉም ተማሪዎች የመሳተፍ እድሎችን ይፈጥራሉ።

### III. ትርጉም

A. የአካዳሚክ ብቃትን የሚጠይቁ የአትሌቲክስ እንቅስቃሴዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ትምህርት ማህበር እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መካከል በተደረገው ድርድር ለአትሌቲክስ ድጎማ ብቁ እንደሚሆኑ ተዘርዝሯል።

B. አማካይ 2.0ማለት በፊተኛው የውጤት መስጫ ወቅት ተማሪው(ዋ) መርሃ ግብር በተያዘለ(ላ)ት ሁሉም ክፍሎች ዝቅተኛው የክፍል አማካይ ውጤት ነው። የተማሪው(ዋ) አጠቃላይ የክፍል ደረጃ አማካኝ ነጥብ (GPA) አይደለም።

C. ማለፊያ ያልሆን ውጤት E እና NC ጨምሮ ተቀባይነት የሌለው የአፈጻጸም ደረጃን የሚያመለክት ማንኛውም ውጤት ነው።

D. ምንም ክሬዲት የሌለው (NC) ማለት የተማሪው(ዋ) የአፈጻጸም ደረጃ ተቀባይነት የለውም ማለት ሲሆን (ለ CR - NC ኮርሶች ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል።)

E. ባለ ብዙ ሰዓት ኮርስ ተማሪዎች በአንድ ሴሚስተር ከ ½ ክሬዲት በላይ የሚያገኙበት ከአንድ ሰዓት በላይ ርዝመት ያለው ኮርስ ነው። ለምሣሌ:- የሥራ ልምድ የሚሠሩ ሥራዎችን፣ የሙያ ልማት ፕሮግራሞችን እና የሁለት ጊዜ የላቀ ምደባ (AP) ኮርሶችን ያካትታሉ።

F. ብቁ የመሆኛ ጊዜ ማለት:- የሪፖርት ካርድ ከተሰጠበት እና የሚቀጥለው የሪፖርት ካርድ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ የሚፀናበት ጊዜ ነው።

### IV. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. ብቁነት

1. ቀደም ባለው የማርክ መስጫ ወቅት ከአንድ ያልበለጠ ያላለፈ(ች)በት ውጤት ጋር 2.0 አማካይ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች በሚቀጥለው የማርክ መስጫ ወቅት ለመሳተፍ ወይም ለመለማመድ በትምህርት ብቁ ይሆናሉ። የብቁነት መመዘኛዎች በሥራ ላይ የሚውሉት በማንኛውም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለተኛ ዓመት የሚገኝ ወይም የምትገኝ ተማሪ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ አማካይ ውጤት ተሞርኩዞ ነው።

   ለብዙ ሰዓት የሚሰጥ ኮርስ እንደ አንድ ትምህርት ይቆጠራል። የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ የክፍል አማካይ ውጤት ሲያሰላ፣ የብዙ ሰዓት ኮርስ ውጤት ለእያንዳንዱ ሰዓት አንድ ጊዜ ይሰላል። ለምሳሌ፡- ኮርሱ የሦስት ክፍለ ጊዜ ኮርስ ከሆነ፣ የማርክ መስጫ ጊዜን አማካይ ለመወሰን ውጤቱ ሦስት ጊዜ መቆጠር አለበት። ሆኖም፣ደብዳቤው ላይ ለብዙ ሰዓታት ኮርስ ውጤት በሪፖርት ካርዱ ላይ አንድ ጊዜ ብቻ ይታያል።

2. በሕጋዊ ሰበብ መቅረት ምክንያት ያልተሟሉ ተብለው ሪፖርት የተደረጉ ውጤቶች እስከሚቀየሩ ድረስ እንደ ማለፊያ ውጤት ይቆጠራሉ። የሪፖርት ካርዶች ከተሰጡ በኋላ በ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ያልተሟሉ ውጤቶች ወደ ማለፊያ ውጤት ደረጃ ካልተለወጡ፣ የብቁነት ዓላማን ለመጠበቅ ውጤቱ እስኪቀየር ድረስ እንደ ወዳቂ ይመዘገባሉ።

3. የተማሪ ኮርስ(ሶች)ን ማቋረጥ/መውጣት

   a) አንድ ተማሪ ኮርስ መውሰድ ከጀመረ(ች) በኋላ በ 25 ቀናት ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ያለ ቅጣት ወይም ሪኮርድ ሳይያዝበ(ባ)ት መልቀቅ ይችላል ወይም ትችላለች።

   b) ለአካዳሚያዊ ብቁነት ዓላማ፤ አንድ ተማሪ ከ 25 ቀናት ቀነ-ገደብ በኋላ ከአንድ ኮርስ በላይ መጣል/መጨመር አይ(ት)ችልም።

   c) አንድ ተማሪ ከ 25 ቀን በኋላ ኮርሱን ሲያቋርጥ/ስታቋርጥ፣ተማሪው(ዋ) ከኮርሱ በሚወጣበት ወይም በምትወጣበት ጊዜ ውጤት ይሰጠዋል/ይሰጣታል። እና ውጤቱ ለትምህርት ብቁነት መመዘኛ ወደ አማካይ የውጤት ደረጃ እንዲገባ ይደረጋል።

4. አንድ ተማሪ ከማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ 25 ቀናት በኋላ ከ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲወጣ/ስትወጣ፣ተማሪው(ዋ) በሚወጣበት ወይም በምትወጣበት ጊዜ የተገኘው ውጤት ለቀጣዩ የስፖርት ወቅት የትምህርት ብቃትን ለመወሰን በጥቅም ላይ ይውላል።

5. አንድ ተማሪ ከ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሸጋገር እና በመቀጠል ወደ MCPS ተመልሶ(ሳ) ሲገባ ወይም ስትገባ፣ ተማሪው(ዋ) ቢያንስ ለአንድ ሙሉ የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ከ MCPS ውጪ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርት የተከታተለ(ች) ከሆነ፣ የትምህርት ብቃትን ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላል። ተማሪው(ዋ) ከ MCPS ውጪ በሆነ ትምህርት ቤት ቢያንስ አንድ የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜን ካላጠናቀቀ(ች) ተማሪው(ዋ) ከተማረ(ች)በት ካለፈው የ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተገኘው ውጤት የትምህርት ብቁነትን ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላል።

6. የሪፖርት ካርዱ በሚሰጥበት ቀን እያንዳንዱ የአትሌቲክስ ስፔሻሊስት ወይም አሰልጣኝ የተማሪው(ዋ)ን ብቁነት ያረጋግጣሉ።

7. አንድ ወይም ሁለት ኮርሶችን ብቻ የሚወስዱ ተማሪዎች ብቁ ለመሆን እያንዳንዱን ኮርስ ማለፍ እና 2.0 አማካይ ውጤት ሊኖራቸው ይገባል።

8. በማንኛውም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ዓመት የመጨረሻ (ሩብ ዓመት) የማርክ መስጫ ወቅት ከአንድ ትምህርት በላይ ሳይወድቁ 2.0 አማካይ ውጤት ከሌላቸው በፎል ወቅት

ብቁ አይሆኑም። ተማሪዎች "D" ወይም ያልተሳካ ውጤት ያገኙበትን ትምህርት በሠመር ትምህርት ቤት ትምህርቱን በመድገም አንድ አራተኛ ማርክ የተሰጠበትን ትምህርት ብቻ ለማካካስ እድሉ አላቸው። ተማሪው(ዋ) "D" ያገኘ(ች)በት ወይም ያልተሳካ ውጤት ካገኘ(ች)በት ከአራተኛው የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ኮርሶች አንዳቸውም በሠመር ትምህርት ቤት ካልተሰጡ፣ ተማሪው(ዋ) በተመሳሳይ የትምህርት መስክ ሌላ ኮርስ እንዲወስድ ወይም እንድትወስድ ይፈቀድለ(ላ)ታል። በተመሳሳይ የትምህርት መስክ ኮርሱ ከሌለ፣ ተማሪው(ዋ) እና የተማሪው(ዋ) ካውንስለር በተገቢው አማራጭ ኮርስ ላይ ሊወስኑ ይችላሉ። ከተገቢው አማራጭ ኮርስ የሠመር ክፍለ ጊዜ የተገኘ ውጤት ዝቅተኛውን የኮርስ ደረጃ አራተኛውን የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ በመተካት የተማሪው(ዋ)ን የብቁነት ሁኔታ ለመወሰን ይተገበራል። የዚህ አማራጭ ኮርስ ውጤት የትምህርት ብቁነትን ለመወሰን ዓላማ ብቻ የሚተካ ሲሆን፤ የተገኘው ክሬዲት በተወሰደው ኮርስ መሠረት ይተገበራል።

B. ልዩ ሁኔታዎች

1. ወደ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገቡ ተማሪዎች ከምዝገባ ወቅት ጀምሮ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ዓመት ቆይታ ድረስ ትምህርታዊ ብቁነት ይኖራቸዋል። ከዚያ በኋላ ብቁነታቸው የሚወሰነው በሰክሽን IV.A.1 እንደተቀመጠው በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ማብቂያ ነው።

2. ከሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በወቅቱ (COSA) ካጸደቀው ካሉበት መጋቢ የትምህርት ቤት ምደባ ውጭ ወደ ሌላ ት/ቤት ለውጥ የሚያደርጉ ከሆነ፤ በሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JEE ድንጋጌ መሠረት፣ ስለ ተማሪ ዝውውር በምዝገባ ከነበረው የተለየ ተጨማሪ የብቁነት መስፈርቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

3. ክሬዲት በሌለው ኮርስ ውስጥ አጥጋቢ ያልሆነ ግምገማ ለተማሪ ብቁነት እንደ ውድቀት አይቆጠርም።

C. የአከባቢ ትምህርት ቤት ኃላፊነቶች

1. ትምህርት ቤቶች የአትሌቲክስ ውድድርን ጨምሮ ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ ያሉትን እድሎች በዝርዝር ለተማሪዎች እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች በጽሑፍ መግለጽ አለባቸው።

2. ተማሪዎች የትምህርት ብቃታቸውን እንዲጠብቁ ወይም ለማሻሻል እንዲረዳቸው ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የሚሳተፉበት ልዩ ልዩ እንቅስቃሴ ሊኖራቸው ይገባል።ይኼውም ኮንትራቶችን ጭምር በትምህርት ቤቶች የሚደረጉ የአትሌቲክስ ውድድሮች፣ የማስጠናት መርሃ ግብሮች፣ የማስተማርና ክትትል የሚያደርጉበት ፕሮግራሞች፣ የካውንስሊንግ እና የክትትል ፕሮግራሞች፣ የአካዳሚክ ድጋፍ ትምህርቶችን እና ምክሮችን መስጠት፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ከትምህርት ሠዓት በኋላ ማስጠናት፣ በትምህርት ሠዓት ወይም ከዚያ በኋላ የሚያጠኑበት አዳራሽ፣ ተማሪዎችን የመድረስ ወይም ሌሎች ፕሮግራሞችን ያጠቃልላል።

3. ትምህርት ቤቶች የድጋፍ ፕሮግራሞቻቸውን ውጤታማነት የሚገመግሙበት ዘዴ ማበጀት ይኖርባቸዋል።

**ተዛማጅ ምንጭ፦ የሜሪላንድ** ደንቦች ኮድ §§13A.06.03.01 እና .02

**የዚህ ደንብ ታሪክ፦ አዲስ** ደንብ ኦገስት 1986፣ ዲሴምበር 1986 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 5 ቀን 1991 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 21 ቀን 1993 ዓ.ም. ማሻሻያ ተደርጓል፣ ዲሴምበር 18 ቀን 1996 ተሻሽሏል፣ ጁን 20 ቀን 2006 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ሜይ 12 ቀን 2010 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 8 ቀን 2021 ማሻሻያ ተደርጎበታል።